# የኢትዮ- ኤርትራ ድርድር ለዘላቂ ሰላምና ልማት ህዝባዊነት ይጠይቃል!

የኤርትራና ኢትዮጲያ ጦርነት መነሻው የድንበር መሳሳብ እንዳልሆነ የኢትዮጵያ መንግስት በተደጋጋሚ ማብራራያ የሰጠበት ስለሆነ ሁሉም ይገነዘበዋል የሚል እምነት አለኝ። ያም ሆነ ይህ ግን ጦርነት ተከሰተ ውጤቱም በሁለቱም አገሮች የሰውና የሀብት ውድመት አስከትሎ የነበረውን በታሪክ የተሳሰረ ህረተሰባዊ ግንኙነት ወደ አላስፈላጊ አእምሮአዊ ቅሬታዎች ገብቶ ወደ ነበረበት ሁኔታ ለመመለስ ከባድ ፈተና ውስጥ ገብቶ እስከ አሁን የደረስንበት ሁኔታ ደርሷል።

የኢትዮጲያ መንግስት ለሰላም ካለው ፍላጎትና ፖሊሲ በመነሳት ቀደም ሲል በታላቁ መሪ ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ አመራር ወቅት የአልጀርሱ የሰላም ድርድር ውሳኔ በመርህ ደረጃ እንደሚቀበለው በአፈጻጸም ደረጃ ግን ህዝቡን ባሳተፈ መንግድ ውይይትና ምክክር እንደሚያስፈልግ ግልጽና በማያሻማ መንገድ የተቀበለው ነው ብቻ ሳይሆን በዚህ ዙሪያ ታላቁ መሪያችን ያደረጉትን ቃለ ምልልስ በ you tube መዳሰስ ይቻላል። ስለሆነም አሁን ያለውን ሁኔታ ምንም አዲስ ነገር እንደሌለውና የነበረውን የኢትዮጵያ የሰላም ውሳኔ ተግባራዊ የማድረግ እርምጃ እንጂ አዲስ ሃሳብ እናዳልሆነ በሰከነ መንገድ መገንዘብ ያስፈልጋል።

ይህንን እንደመነሻ ካልኩኝ አሁን ባለው የኢትዮ- ኤርትራ የሰላም ፍላጎት በሁለቱም መንግስታት በኩል ላሳዩት ለሰላም ያላቸውን ዝግጁነት ምስጋና የሚቸራቸው ነው የሚል እምነት አለኝ ሆኖም ግን አሁንም ቢሆን ይህንን የሰላም ፍላጎት የተሟላና የሁለቱም አገሮች ህዝቦች ከማንኛውም መቃቃር በመውጣት በጋራ የመልማትና፣ የማደግ ፍላጎታቸው እንዲሟላ የተጀመረውን የሰላም ጮራ ህብረተሰቡ በባለቤትነት መንፈስ ተግባራዊ ለማድረግ ብዙ የሚቀር እንዳለ በመረዳት ሰፊ ስራ ለመስራት ***ቁልፍ ጉዳይ የሰላሙ ፣የድንበሩ ባለቤት ህዝቡ መሆኑ ማመንና ተግባራዊ ማድረግ በቅድሚያ መታየት ያለበት ነው።***

ስለሆነም አሁን የተፈጠረውን የሰላም ድባብ ከማንኛውም ንክኪ በመውጣት ወሳኙ ህዝቡ ነውና ሁለቱም መንግስታት ዋናውን የድንበር የማካለል ስራ ለህዝቡ ቢሰጡት ይህ ማለት አሁን ያለውን በኢትዮጲያ ድንበርም ሆነ በኤርትራ ድንበር ያሉ ህዝቦች ስጋታቸውን በተለያየ መንገድ ሲገልጹ ይታያል። ከዚህ ስጋት መውጣትና የሚቻለው በድንበሩ ያለውን ኢትዮጲያውያንም ሆነ ኤርትራውያን መሬታቸው ከማንኛውም የመንግስት አካል በላይ በሚገባ የሚያውቀው፣ የሚረዱትና፣ የሚኖሩበት ሰላምም የሚያምኑ እንደመሆናቸው መጠን ***"ሁለቱም መንግስታት ከዚህ የድንበሩ ማካለል ጉዳይ በመውጣት በድንበር አካባቢ ያሉ የሁለቱም አገሮች ህዝቦች በህዝብ ለህዝብ ትስስር አፈፃፀም መሰረት ሙሉ በሙሉ የሚስማማቸውን የውሳኔ ሃሳብ ለሁለቱም መንግስታት በነጻ ህሊናቸው በማሰቀመጥ እንድያቀርቡ"*** ሙሉ ዕድል ተሰጧቸው ስራው እንዲያከናውኑት ቢደረግ የተሟላ ሰላም በማረጋገጥ ዘላቂ ልማት በማረጋገጥ አብሮ የማደግና የመልማት ፍላጎታቸውን እውን እንዲሆን ትልቅ ህዝባዊነት ይጠይቃል የሚል እምነት አለኝ ብቻ ሳይሆን የብዙ ህዝቦች ፍላጎትም መሆኑ ታውቆ ከወዲሁ ቢታሰብበት እላለሁ።

**ዘላቂ ሰላምና ልማት በተሟላ ህዝባዊነት ይረጋገጣል!!**

**ካሳሁን ነኝ**

**ከአዲስ አበባ**